# ትንሹን መለስ ዜናዊ እንተዋወቅ

ዳግማዊ ጉዱ ካሣ

መለስ ዜናዊ አለመሞቱን ይሄ ፌስቡክ የሚሉት ጣጠኛ ነገር አረዳኝ፡፡ ትልቅ መርዶ ነው በውነቱ፡፡ ይህች ሀገር የቀልዶች ምድር እየሆነች ነው፡፡ ዕድገትና ሥልጣኔ በመተካካት ዘይቤ እየዘመነ ወደፊት ይሄዳል እንጂ ድንቁርናና ዕብሪት፣ ዘረኝነትና አምባገነንነት እንዴት ይተካካል? "ለአርጂ አይከብደው"ም መቼም፡፡ እናም ይሄ ፌስቡክ መጥፎ መርዶ አርድቶ ያለፈች የግንቦት ሰባት ወደ ስምንት ሌሊቴን አበላሸብኝ - ይቺ ግንቦት ሰባትና ስምንት ጠምሳኛለች፡፡ ከመረጃ መራቅ ምንኛ ዓለም ነው ግን? አትሰማ አትለማ ዝም ብለህ ትኖራለህ፡፡ ያንንም ይህንንም ልከፈት ካልክ ግን ስትበግን መዋልና ማደርህ ነው - ለክ እንደኔ፡፡ የተኙ እንዴት ያስቀናሉ? ከርሳቸውን ከመሙላት ባለፈ ስለሀገር የማይሞቃቸው የማይበርዳቸው ድንዙዛን እንዴት የታደሉ ናቸው! ኬሬዳሽ!

እጅግ ከመናደዴ የተነሣ ሌሊቱ ነግቶልኝ ይህችን ማስታወሻ እስክጽፍ ቸኮልሁ፡፡ ደግሞም የምጽፍበት ርዕስ አበዛዝ! የቱን ትቼ የቱን ልያዝ? ግን ዕድሜ ለባለቤቴ ማንጠግቦሽ፡፡ ከላይ ያስቀመጥኩትን ወደደችልኝ፡፡ እንጂ እኔማ ....

- "ወጣ ወጣና እንደሽምቀ ተንከባለለ እንደሙቀጫ - አብርሃ ደስታ"
- "የት ይደርሳል ያሉት ጥጃ ሉካንዳ ቤት [ሲልከሰከስ?] ተገኘ - አብርሃ ደስታ"
- "ያመኑት ፈረስ ጣለ በደንደስ - አብርሃ ደስታ"
- "የመጥረቢያ ልጅ መዘለፊያ - አብርሃ ደስታ"
- "የዘሬን ብተው ያንዘርዝረኝ -አብርሃ ደስታ"
- የመለስ ዜናዊን ሌጌሲ አስቀጣይ ወጣቱ አብርሃ ደስታ"
- "የሌባ ተቀባዩ አብርሃ ደስታ"
- "በጊዜ የጮኸ ጅብ አያሳድረኝም - አብርሃ ደስታ"
- "እባብ የወጣበትን ጉድጓድ አይስትም - አብርሃ ደስታ"
- ጉድ ያለው ገንፎ አድሮ ይፋጃል - አብርሃ ደስታ"
- "ጉድ ሳይሰማ መስከረም አይጠባም - አብርሃ ደስታ"
- "ትልቁ ዳቦ ሊጥ ሆነ ..." ....

በሚሉ በርካታ አማራጭ ርዕሶች ውስጥ ተዘፍቄ መከራየን እያየሁ ነበር፡፡ ማንጠግቦሽዬን ልጅ ይውጣላት ይስጣት - ገላገለችኝ፡፡

በወያኔ ታስሮ "ፍዳውን ሲያይ" እንደነበረ የሚነገርለት የአረና ፓርቲ ሊቀ መንበር አብርሃ ደስታ በፌስቡክ ገጹ ወልቃይትን በሚመለከት ያሠፈረውን የማይነቃነቅ አቋም አነበብኩ፡፡ ይህ የሕወሓት አቋም የአረና ትግራይ አቋምም መሆኑን በዋና ሊ/መንበሩ አማካይነት በመገለጡ ምክንያት ተገንዘብኩ - ብዙውን ጊዜ "ተከተል አለቃህን ...." ምናምን ስለሚባል ከዋና አለቃ የሚወጣ ምንዝር የመኖሩ ዕድል ጠባብ ነውና የአረና አባላት ከዚህ ልጅ አቋም የተለዩ አቋም ይኖራቸዋል ብሎ መገመት ያስቸግራል፡፡ ስለዚህ አረናና ሕወሓት እኔ ከማላውቃቸው መለስተኛ ልዩነቶች ባሻገር በዋና ዋና ዓላማዎች ይህ ነው የሚባል ልዩነት እንደሌላቸው ተገንዝቤያለሁ፡፡ ስለሆነም አረና ቁጥር ሁለት ካስፈለገም ሦስት ሕወሓት ሊሆን ነው - በኔ ዕይታና ግንዛቤ፡፡ ገና የተረገዙ ችግሮች አሉ ማለት ነው፡፡

የትግራይ ሕዝብ በቁጥርና በጊዜ ቅደም ተከተል በሚለያዩ "ሕወሓቶች" እየተመራ ይቀጥላል ወይንስ አይቀጥልም የሚለውን የራሴን ጥያቄ ጊዜ እንደሚመልስልኝ አልጠራጠርም፡፡ ለአሁኑ ግን አብርሃ ደስታ የሕወሓት የወጣት ክንፍ ወካይና ዓላማውን አስፈጻሚ መሆኑን መረዳቴን ገልጬ ከዚህ በታች ከተቀመጠው የወጣቱ ፖለቲከኛ የዳግማዊም ይባል የሣልሣዊ ሕወሓት አባል አቋም ጋር እንዲታይልኝ እፈልጋለሁ፡፡ አዎ፣ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ነው ያለነው፡፡ በፖለቲካ የሚናቅ ነገር የለም፡፡ የዛሬ ትንሽ የነገ ትልቅ ነውና!

> የአማራ አክቲቪስቶች ስለ አማራ ህዝብ ብቻ ቢቀረቀሩ አይገርምም፤ ያው ሁሉም ወደ ራሱ ብሄር መቆርቆር ገብቷልና። ከአማራ ብሄርተኞች ጋር ያልተግባባሁበት ነጥብ የወልቃይት ጉዳይ ነው። ከአስር ልፈታ አካባቢ "የወልቃይት ጥያቄ" መነሳቱ ነገሩኝ። የግዛት መስፋፋት ጥያቄ እንደማያዛልቅ ነገርኳቸው። አልተግባባንም። ወልቃይትን የጦር ሜዳ ከማድረግ የዘለለ ነገር እንደማይኖረው ነግርያቸው ተለያየን። የሀገር አንድነት ይቀድማል ከሚል እሳቤ እና ይታረማሉ ከሚል ተስፋ ***<u>በትዕግስት ለማለፍ ሞከርኩኝ</u>***። ***<u>ጠቅላይ ሚኒስተር ዶር አብይ አሕመድ ከባህርዳር ሰዎች ጋር ሲነጋገር የተነሱ ጥያቄዎች ስሰማ ተገረምኩኝ</u>***። አሁን ደግሞ ጋዘጠኛ ተመስገን ደሳለኝ ጎንደር ሂዶ "ወልቃይት እንደ ካሽሚር" በሚል ርእስ ***<u>የአማራ አክቲቪስቶች ትግል የነፃነት ሳይሆን የግዛት ማስፋፋት እንደሆነ በግልፅ ቋንቋ አስረድቷል</u>***። ***<u>ዓላማቸው ወልቃይትን የጦር አውድማ በማድረግ ትግራይን ማዳከም ነው</u>***። **እኔም እላለሁ፡** ***<u>ወልቃይትን የጦር ሜዳ ማድረግ ይቻል ይሆናል፤ ወልቃይት መውሰድ ግን ከቶ አይቻልም</u>***። የየትኛውም ህዝብ የነፃነት ጥያቄ እደግፋለሁ፤ የግዛት ማስፋፋት ጥያቄ ግን አናስተናግድም። ኢትዮጵያ Plan B ያስፈልጋታል። ***<u>ትግራዋይ ሕብር ተወደብ!</u>*** It is so!!! (አፅንዖት የተጨመረ)

ተመልከቱት ይህን "ጩጬ" አምባገነን! ታዲያ መለስ ዜናዊ ሞቷል አልሞተም? በጭራሽ አልሞተም! ይህ ወጣት ትግራዋይ አንድ ትልቅ ፓርቲ እየመራ ይህን የመሰለ አቋም የሚያራምድ ከሆነ ሌላውና ከርሱ በታች ያለው ታዳጊ ክፍልማ እንዴቱን ያህል በሕወሓት ስብከት አይመረዝ? የዩንቨርስቲ ምሁሩ በተቀማ መሬትና በተዘረፈ ሀብትና ንብረት እንዲህ በስሜት ከራዠና ከተወራጨ ማይሙማ ከርሱ እንዴት አይብስ? አብርሃ ደስታ ከራስ ሥዩም መንገሻ ይልቅ የትናንቱ ሕወሓት አማልሎት ታሪክን በጂዶ ሲዘርረው እያየን ነው፡፡ አብርሃ ደስታ ከታሪክ ማኅደር ይልቅ የዛሬ የትግራይ በሰው ሀብትና መሬት መክበር ኅሊናውን አሳውሮት ራሱ ታውሮ ታናናሾቹን ሊያሳውር እንዴት እንደሚራወጥ እያስተዋለን ነው፡፡ አደብ እንዲገዛ የሚመክረው ሰው ቢያገኝ ለሁላችንም በተለይም ለትግራይ ይበጃል፡፡ እነአብርሃ በልባቸው ያሸመቁት የተለዩ ፍላጎት ከሌለ በስተቀር ወልቃይትና ራያ ይቅሩና ኢሉባቦርና ቦንጋም የትግራይ ናቸው - ትግራይም የአማራና

የሌላው፡፡ የምሁር ማይሙ አብርሃ አላስተዋለውም እንጂ በአሁኑ ወቅት ተጋሩ የት የት እንዳሉ እንኳን ቢረዳ በአንዲት የሰው ንብረት እንዲህ ግምት ውስጥ ባልገባ ነበር - አብርሃን ልጠይቀው - ትግራይ ውስጥ ስንት ትግሬዎች አሉ ለመሆኑ? በጣም ጥቂት ናቸው፡፡ ችግራችን የአገዛዝ እንጂ የመሬት ጥበትና ስፋት አይደለም፡፡ ፍቅርና መልካም አስተዳደር ካለ ማንኛውም የኢትዮጵያ መሬት የሁላችንም ነው፡፡ ይቺ ንጥቂያ ሌላ ዓላማ አላት፡፡ “ተጋሩ ተባበሩ፤ ተደራጁ፤ ነገሩ እንዲህ ነው” የሚያስብል ምንም ነገር የለም፡፡ አብርሃ ወደ ኅሊናው እንዲመለስ እመክረዋለሁ፡፡ ትግራይ ሕወሓት የደገሰላት ይበቃታል፤ በመጀመሪያ እርሱን ትወጣው፡፡ “በፋሲካ የተቀጠረች የቤት ሠራተኛ ሁል ጊዜ ፋሲካ ይመስላታል” እንዲሉ አብርሃ ለወግ ለማዕረግ በደረሰበት ዕድሜው የሚያያት ትግራይ እንዳለች ትቀጥላለች ማለት እንዳልሆነ አብርሃ ብቻ ሣይሆን ሁሉም ሊረዳው ይገባል - በእግረ መንገድ የነገሮችንና የሁኔታዎችን መለዋወጥ ተፈጥሯዊ ባሕርይ ለመጠቆም እንጂ ይህ በፍጹም ማስፈራራት አይደለም፡፡ የእውነትን መንገድ ብቻ ከተከተልን ግን ኢትዮጵያ የኢትዮጵያውያን ሁሉ ናት! በቃ፡፡ በብጫቂ መሬት የከት ጠባያችንን አናሳይ፡፡ ወጣቱ ትውልድ በተለይ የኣባቶቹን ስህተት ማረም ይገባዋል እንጂ ማባባስ የለበትም፡፡ አብርሃ አይዞህ - ወያኔ ቢወድቅ ሁመራ ላይ ቤትህን ሠርተህ የጥጥ አዝመራህን እያዘመርህ በአባትህ ስም በደስታ ትኖራለህ፡፡ አትስጋ፡፡ አሁን ግን ይህን የሳይከካ ተቦካ ዛቻና መስፈራርቾህን ተወው፡፡ እሳት ላይ የተጣደ ድስት በጭስ አይደነግጥም፡፡ አማራው ለመብቱ እየታገለ ባለበት በአሁኑ ወቅት አንተም መንከራ ልትጨምርለት “አለሁ!” ማለትህ ከትዝብት ውጪ ምንም አያስገኝልህም፡፡ ለዜና ሀተታና ለሚዲያ ፍጆታነት ለሚው መርሐ ግብር (ፕሮግራም) እንጂ ለመከራ backlog ሊኖረው አይገባምና ያቺን Plan B ምንትስ የምትላትንም መጠባበቂያ የጦርነት ዕቅድ አስብባት፡፡ ብሃቲሩ አቅል ግዛ፡፡ “ትግራዋይ ሕበር ተወደብ” ሣይሆን “ኢትዮጵያውያን ሕበሩ ተወደቡ” በል፡፡ ዕደግልን፡፡ ባለህበት አትርገጥ፡፡ መለስን እርሳው፤ ያረጁ ያፈጁ ሽማግሌ ጓደኞቹንም እርሳቸው፡፡ በመለስ ጥቂት ጊዜ መግነን ይቻላል፡፡ በመለስ ሌጋሲ ባለሰማይ ጠቀስ ፎቅና ባለሮልስ ሮይስ መሆን ይቻላል፡፡ በመለስ ሌጋሲ ትግራይን እስክታብጥና እስክትፈነዳ ድረስ ሀብታምና ኖልቁ መሣፍርት የሌለው ንብረት መጋዘን ማድረግ ይቻላል፡፡ .... ግን ዳፋውን ልጅ ነህና ስለማይገባህ ላንተ አልነገርህም፡፡ ዕድሜህ ገና ስለሆነም የመለስን ጦስ ጥምቡስ አንተም ልታየው ትችል ይሆናል፡፡ ነቢይ አይደለሁም፡፡ ይችን የመለስንና ያንተን መሰሉን የትዕቢትና የዕብሪት አካሄድ የመጨረሻ ውጤት መናገር ግን አያቅተኝም፡፡ እኔ ብቻ ሣልሆን የልጄ ልጅም ይነገርሃል - ልጄ፡፡ ይህች ብልጭልጭ ዓለም ኅሊናን ታስታለች፤ ፈተናዋን በሚገባ መሥራት የሚችሉና የሚያልፉም በጣም ጥቂቶች ናቸው፡፡ አንተ ለምሣሌ ወደቅህ፡፡ በተዘረፈ መሬት ማምለክህ አንዱ የመውደቅህ ማሳያ ነው፡፡ ግን ለንስሃ ጊዜ አለህና ወደራስ - ወደ ውስጥህ ግባ፤ ሁሉም ደግሞ ያልፋል፡፡ ሃይማኖትም ይኑርህ ታዲያ የኔ ዓለም፡፡ ሰው የሃይማኖት ልጓም ከሌለው ፍላጎቱ ልክ እንዳንተና መሰሎችህ ገደብ ያጣል፡፡ ...

ይህ ወጣት አምባገነን ዛሬ ከሥልጣንና ከሀብት ሩቅ ሆኖ እያለ ልክ እንደሙሶሊኒ በትዕቢት እንዲህ ከደነፋ ነገ ዕድል ገጥሞት የጠበንጃ ግምጃ ቤቱን ቁልፍ ቢረከብ በተለይ በአማራውና በወልቃይት ቀደምት ነዋሪዎች ላይ የመርዝ ጭስ እንደማያርከፈክፍ ምንም ዓይነት ማረጋገጫ የለንም፡፡ መፍራት ታዲያ ይህንና ከአሁኑም ነው፡፡

## እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ከአሁንና ከወደፊት ግልገል ፋሽስቶችም ይጠብቃት!!